# የማሽነሪ እና ተሽከርካሪ ኪራይ አገልግሎት ግዥ

## ግልጽ የጨረታ ማስታወቂያ

### (የግዥው መለያ ቁጥር-ERC/BDD/EP/B025/2025)

የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን አቦቦ-መቲ/ ኩቢቶ ማዞሪያ-መቲ መንገድ ጥገና(ጋምቤላ) እና UNISA-GELAN-BISHOFTU-BIYO(ቢሾፍቱ) መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክቶች የሚያገለግሉ የተለያዩ የኮንስትራክሽን ማሽነሪዎችን እና ተሽከርካሪዎችን በጨረታ አወዳድሮ መከራየት ይፈለጋል፡፡ ስለሆነም የሚከተሉትን መመሪያዎች መሠረት በማድረግ በጨረታዉ እንዲወዳደሩ ተጋብዘዋል፡፡

1. በዘመኑ የታደሰ ህጋዊ የጸና ንግድፈቃድ ያላቸው፤
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ያላቸው፤
3. የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ፤ የሰርቪስ መኪና በኪራይ ለማቅረብ ግን የቫት ተመዝጋቢ የሆኑና ያልሆኑ መወዳደር ይችላሉ ተጫራቾች በጨረታ ለመሳተፍ ከላይ ከተራ ቁጥር1-3 የተጠቀሱትንና የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሰነዳቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
4. የሚቀርቡት ተሽከርካሪዎች በሙሉ የፈረስ ጉልበታቸው፣ የስሪት ዘመናቸዉና ሌሎች ከጨረታ ሰነዱ የተገለፁት መስፈርቶች ተሟልተዉ መቅረብ አለባቸው፡፡
5. የኪሎ ሜትር እና የነዳጅ ቆጣሪው በትክክል የሚሰራ መሆን አለበት፡፡
6. **ሎት 1.** ***ለአቦቦ-መቲ/ ኩቢቶ ማዞሪያ-መቲ መንገድ ጥገና ፕሮጀክት የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች(ሎቤድ፣ ዶዘር ኤክስካቫተር፣ግሬደር ፣ሎደር፣ውሃ ቦቴ፣ነዳጅ ቦቴ፣ሮለር፣ገልባጭ መኪና እና ሰረቪስ ፒካፕ ሲሆኑ)***

- **ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (ቢድ ቦንድ) ለሎት 1. *ለአቦቦ-መቲ/ ኩቢቶ ማዞሪያ-መቲ መንገድ ጥገና ፕሮጀክት* 100,000.00 በባንክ በተረጋገጠ ክፍያ ትዕዛዝ (ሲፒኦ) ወይም ጨረታ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ለ60 (ስልሳ) ቀናት የሚቆይ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ብሄራዊ ባንክ እውቅና ከሰጣቸው ባንኮች ብቻ ማቅረብ አለባቸዉ፡፡**

**ሎት 2.** ***UNIS-GELAN-BISHOFTU-BIYO መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት የሚያስፈልጉ ማሽነሪዎች እና ተሽከርካሪዎች (አስፋልት ፔቨር፣ታየር ሮለር፣ደብል ድረም ሮለር፣ደብል ድረም ሚኒ ሮለር እና ኮንክሪት ከርብ ማስሪያ ማሽን ሲሆኑ)***

- **ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና (ቢድ ቦንድ) ለሎት 2. *UNIS-GELAN-BISHOFTU-BIYO መንገድ ማሻሻያ ፕሮጀክት* 100,000.00 በባንክ በተረጋገጠ ክፍያ ትዕዛዝ (ሲፒኦ) ወይም ጨረታ ከተከፈተበት ቀን ጀምሮ ለ60 (ስልሳ) ቀናት የሚቆይ በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና ብሄራዊ ባንክ እውቅና ከሰጣቸው ባንኮች ብቻ ማቅረብ አለባቸዉ፡፡**

7. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 500.00 /አምስት መቶ ብር ብቻ/ በመክፈል ከገንዘብ ያዥ ቢሮ ቁጥር -_32_ ይህ ማስታወቂያ አየር ላይ ከዋለበት ቀን ከ29/10/2017 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 21/11/2017 ዓ.ም(ጨረታው እስከሚዛገበት) በኮርፖሬሽኑ መ/ቤት በአካል በመገኘት ዘወትር በስራ ስዓት መግዛት ይችላሉ፡፡

ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ማስከበሪያውን፤ ፋይናንሻልንና ቴክኒካሉን ሰነዱን በጥንቃቄ በታሸገ አንድ ፖስታ በማድረግ የግዥ ኦፊሰሮች ቢሮ በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ዘወትር በስራ ሰዓት ጨረታው ከወጣበት ዕለት ጀምሮ እስከ 21/11/2017 ዓ.ም ጠዋት 4.00 ስዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡

ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በኮርፖሬሽኑ የመሰብሰቢያ አዳራሽ በ21/11/2017ዓ.ም ከቀኑ4፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ በ4፡30 ስዓት ይከፈታል፡፡ እለቱ የስራ ቀን ካልሆነ በቀጣዩ ቀን በተመሳሳይ ሠዓት ይከፈታል፡፡

8. መስሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
9. በጨረታው ለመሳተፈ የሚፈልጉ ስለጨረታው ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ በፋክስ ቁጥር +251114702044- በመልክ ወይም በስልክ ቁጥር 0114702058 ወይም0114702051 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፡፡

***(አድራሻ- የኢትዮጵያ ምድር ባቡር ኮርፖሬሽን ፣አዲስ አበባ(ሴራሊዮን መንገድ /መሿለኪያ)፣ስልክ --0114702058/0114702051/0966800400፣ፋክስ --+251114702044 ኢሜል -erailways@erc.gov.et, bethel_erc_eng_procur@erc.gov.et)***